# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 231 ጥቅምት 8 2005 ገጽ 1

በአዲስ አበባ ሌሎች ከተሞች እጅግ ዘመናዊ ህንፃዎችን እየገነቡ ሃገሪቷ በእርግጥም ያለፈላት እንዲመስል እያደረጉ ያሉት በብድርና በፕራቬታይዜሽን ሃብታም እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው በዘራቸው የተመረጡ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ናቸው። ብዙዎቹ ከሃያ ዓመት በፊት አንዳችም ሃብት ያልነበራቸው ሰዎች ናቸው፤ ዛሬ ግን ሚሊዮንን ተሻግረው ቢሊየነር የመሆን ህልም ውስጥ ገብተዋል። የእነዚህ ሰዎች የሃብት ምንጭ ከታታሪነትና ከፈጠራ ጋር ምንም ዝምድና የለውም። እነዚህ በሕዝብና በመንግሥት ንብረት የወፈሩ መዥገሮች ናቸው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ በሙስሊም ሃይማኖት ውስጥ የሚያደርገው ጣልቃ ገብነት ተወገዘ። በቀበሌ የተደረገው የሃይማኖት መሪዎች ምርጫ ተቃውሞ ገጥሞታል

አርብ ጥቅምት 9 ቀን በአዲስ አበባ፣ በደሴ፣ በከምሴ፣ በባቲ፣ በድሬዳዋ፣ በሃረር፣ በጅማ እና ሌሎችም በርካታ የኢትዮጵያ ከተሞችና ገጠሮች የሚገኙ ሙስሊሞች ተቃውሞዓቸውን አሰምተዋል። በአዲስ አበባ አንዋር መስጊድ የተገኘው ሕዝበ ሙስሊሙ ብዛት በመቶ ሺዎች የሚቆጠር መሆኑ በቦታው የነበረው ዘጋቢያችን ገልጾልናል።

የትናንትና አርቡ ተቃውሞ ወያኔ ያቀነባበረው የውሸት የመጅሊስ ምርጫ ተደረገ ከተባለ ከመስከረም 27 ወዲህ የተደረገ የመጀመሪያ ታላቅ ሕዝባዊ ተቃውሞ መሆኑ ምሳሌነቱ ከፍተኛ ነው ተብሏል። የሕዝበ ሙስሊሙ በዚህን ያህል ብዛትና በመላው አገሪቱ ተቃውሞው ማሰማቱ መስከረም 27 የተደረገው ምርጫ የሕዝበ ሙስሊሙ ድጋፍ የሌለው መሆኑን አቢይ ምስክር ነው ተብሏል።

ዘጋቢያችን በአንዋር መስጊድ አግኝቶ ያነጋገራቸው አቶ ያሲን ከማል "ከምርጫው በላይ ያበሳጨኝ የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ተብዬ ኃይለማርያም ደሣለኝ ንግግር ነው" ካሉ በኋላ "ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ' እንደሚባለው አፉን በእኛ ላይ አሟሸብን" ብለውታል በቁጭት እየተንገበገቡ። እንደ አንዋር መስጊድ ሁሉ በኑር መስጊድ የተገኘውም ሕዝበ እጅግ ብዙ እንደነበር የደረሱን መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ለመብቶታቸው መከበር በተደራጀ ሁኔታ መታገል ከጀመሩ ዓመት ሊሞላቸው የተቃረበ ሲሆን በሰላማዊ መንገድ ለሚያቀርቡት ጥያቄ ወያኔ የሰጣቸው (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ኢትዮጵያ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ሰዎች በብዛት ከሚገኙባቸዉ ሦስት የአፍሪካ አገሮች መካከል አንዷ መሆኗን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም በቅርቡ ባወጣዉ ጥናታዊ ሪፖርት ይፋ አደረገ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት መርሀግብር በታዳጊ አገሮች ዉስጥ አካሂዶ በቅርቡ ይፋ ባደረገዉ ጥናታዊ ዘገባ መሠረት ኢትዮጵያ ማንበብና መጻፉ የማይችልዩ ሰዎች በብዛት ከሚገኝባቸዉ የመጨረሻዎቹ የአለም አገሮች ዉስጥ ከማሊና በቅርቡ ነጻነቷን ከተቀዳጀችዉ ደቡብ ሱዳን ቀጥላ በሦስተኛናት ደረጃ ላይ ትገኛለች ብሏል። በዚህ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት መርሀግብር ጥናት መሠረት ከአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ህዝብ ዉስጥ ማንበብና መጻፍ የሚችለዉ 28 በመቶዉ ወይም 25 ሚሊዮን ህዝብ ብቻ እንደሆነ ታዉቋል። ኢትዮጵያ በአፍሪካ ዉስጥ በህዝብ ብዛት ሁለተኛ እንደሆነችና 90 ሚሊዮን ህዝብ እንዳላት መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በጥናቱ ዉስጥ ከተካተቱት 184 የአለማችን ታዳጊ አገሮች ዉስጥ ሁሌ ስማቸዉ በድህነት ተርታ የሚነሳዉ ኒጀር፣ ቡርኪናፋሶና ቻድ መሀይምነትን በማስወገድ ከኢትዮጵያ በላይ የተቀመጡ ሲሆን ኢትዮጵያ ከ184ቱ አገሮች ዉስጥ 182ኛ ደረጃ ላይ ተመድባለች። በዚህ ምደባ መሠረት ባለፉት ሃያ አመታት መንግስት አልባ ሆና የከረመችዉ ሶማሊያ የአፍሪካ የእድገት ምልክት ናት ተብሎ ከተሰበከላት ኢትዮጵያ ሁኔታ ህዝቧን ማስተማር መቻሏ የአለም ባንክና ሌሎች እርዳታ ሰጪዎችን ጨምሮ ብዙዎችን እያነጋገረ ነዉ።

የወያኔ ባለስልጣኖች በተደጋጋሚ ጸረ ህዝብ ለመሆኑ በምሳሌነት የሚጠቀሙት የደርግ ስርአት እንኳን 60 በመቶ ኢትዮጵአዉያንን ከመሀይምነት በማላቀቁ አለም አቀፍ ሽልማት መሸለሙ የሚታወቅ ሲሆን ይህ ቁጥር ዛሬ ወደ 28 በመቶ ማሽቆልቆሉ የወያኔን የትምህርት ፖሊሲ ከፍተኛ ጥያቄ ዉስጥ ከትቶታል።ከፍተኛ የአሜሪካና የአዉሮፓዉ ህብረት ባለስልጣኖች ለኢትዮጵያ የሚሰጠዉ የዉጭ ብድርና ዕርዳታ አብዛኛዉ የሚዉለዉ ለጤናና ለትምህርት ዘርፎች ነዉ እያሉ ቢናገሩም ሀያ አመት ሙሉ የሰጡት ዕርዳታና ወያኔም በአስር እጥፍ አሳድግያለሁ የሚለዉ የትምህርት ተቋማት ብዛት መሐይምነትን ለመቅረፍ ያደረገዉ ምንም አስተዋጽኦ አለመኖሩ ብዙ ታዛቢዎችን ያሳሰበ ጉዳይ ሆኗል።

## በወያኔ ዕስር ቤት ለ13 ወራት ታስረው የነበሩ የስውዲን ጋዜጠኞች የቃሊቲ እስር ቤት በአይጦች፣በነብሳትና በተባዮች የተበከለ መሆኑን አጋለጡ

እስር ቤቱ ኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና ጋዜጠኞችም የታሰሩበት ስፍራ እንደሆን የገለጹት ስዊዲንዊያኑ ጋዜጠኞች ክልሉ መያዝ ከሚገባው ከሁለት እጥፍ በላይ እስረኞች የታጎሩበት፣ የሚጋረፍ ወበቅ ያለበትና ሳምባ ነቀርሳን የመሳሰሉ ተላላፊ በሽታዎች ችግር የሚስተዋልበት ፍጹም ሲኦል የሆነ ቦታ እንደሆነ አብራርተዋል።

ጋዜጠኞቹ ለቢቢሲ እንዳሉት ወደዚህ ሲኦል እስር ቤት ከመወርወራቸው አስቀድሞ ከፍተኛ ስቃይ ማየታቸውን ገልጸው ወንጀለኛነታቸውን ለማሳየት በሶማሌ ክልል ምክትል ፕሬዘደንት ዳይሬክተርነት ፊልም አዲሰሩ ከተደረጉ በኋላ ይሄንኑ ፊልም ፍርድ ቤቱ በማስረጃነት በመጠቀም በአስራ አንድ ዓመት እስራት እንዲቀጡ ወሰናባቸዋል።

በፊልሙ ቀረጻ ወቅት የሶማሌው ክልል ም/ፕሬዘደንት የተሰጣችሁን ሽብርተኛና ወንጀለኛ ነን እያሉ የሚናዘዙትን ባህሪ በደንብ አልተጫወታችሁም በማለት እንደገና እንዲለማመዱ በማድረግ በሁለት የተለያዩ ቦታዎች እንዳስቀረጻቸውም ተናግረዋል።

የፍርድ ቤቱ የችሎት ሂደት ጨዋታ ነበር ያሉት ስዊዲናዊያኑ ማርቲን ሽብዬና ጆሃን ፐርሰን የወንጀለኝነቱን ብይን ፍርድ ቤቱ ከመስጠቱ ሃያ ቀናት በፊት በቴሌቪዥን የሰጠው መለስ ዜናዊ ነበር ብለዋል።

## በወያኔ አገዛዝና በኦጋዴን ነፃነት ግንባር መካከል ናይሮቢ ዉስጥ ተጀምሮ የነበረዉ የእርቅ ንግግር ዉጤት አልባ ሆኖ መክሸፉን የወያኔ ባለስልጣኖች አመኑ

በኬንያ መንግስት አስተባባሪነት እዚያዉ ኬንያ ናይሮቢ ዉስጥ በወያኔ አገዛዝና በኦጋዴን ነፃነት ግንባር መካከል ተጀምሮ ሲካሄድ የነበረዉ የእርቅ ንግግር ያለ ምንም ዉጤት መጠናቀቁን አንድ የወያኔ አገዛዝ ቃል አቀባይ አዲስ አበባ ዉስጥ በሰጠዉ መግለጫ አስታወቀ።

በጀኔራል መሐመድ ኡስማን ከሚመራዉ የኦብነግ አንደኛዉ ክንፍ ጋር በመከላከያ ሚኒስትሩ በሲራጅ ፈረጃ ተወክሎ ሲደራደር የነበረዉ የወያኔ አገዛዝ ለድርድሩ መክሸፍ ምክንያት የሆነዉ የኦብነግ ህገ መንግስቱን ተቀብሎ በህገ መንግስቱ ስር ለመስራት ፈቃደኛ አለመሆኑ ነዉ ያለ ሲሆን ኦብነግም በበኩሉ የወያኔ አገዛዝ ለዉይይት የማያመቹ ደንቃራ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን በመደርደር የጋራ ዉይይቱ እንዳይሳካ ሆን ብሎ ችግር ፈጥሮአል ብሎአል።

የዉይይቱን መርሀ፤ ሞዳሊቲና አጀንዳ የቀረጸዉ የድርድሩ የመጀመሪያዉ ክፍል በአጥጋቢ ሁኔታ መጠቃለሉን የገለጹት የኦብነጉ አቶ አብዱራሂም ማህዲ ሁለተኛዉ ዙር ድርድር ሲጀመር የወየኔ አገዛዝ የገባዉን ቃል መስበሩንና ከዚህ በፊት እንደሚያደርገዉ ድርድሩን እሱ ወደሚፈልገዉ አቅጣጫ ብቻ ለመዉሰድ በመፈለጉ ዉይይቱን ለማቋረጥ ተገድደናል ብለዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የወያኔ አገዛዝ በፕራይቬታይዜሺን ስም ለግል ባለኃብቶች በሚሸጣቸዉ የአገርና የህዝብ ንብረት አገሪቱ ተጠቃሚ እንዳልሆነች እየተነገረ ባለበት ወቅት ወያኔ የአዶላ ወርቅ ማዕድን ማምረቻን ለመሸጥ መወሰኑ ተሰማ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ባለፉት ሃያ አንድ አመታት በፕራይቴዚሺን ስም ለግል ባለ ኃብቶች በሸጣቸዉ የህዝብና የአገር ንብረቶች ተጠቃሚ የሆኑት የህወሀት ፓርቲና የሼክ አላሙዲን ኩባንያዎች እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ ንብረቱ ሲሸጥ ቁጭ ብሎ ከመመልከት ዉጭ በሽያጩ ተጠቃሚ እንዳልሆነ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ።

ወያኔ ሥልጣን ከተቆጣጠረ የመጀመሪያው ሁለትና ሶስት አመት ጀምሮ ቀደም ሲል በህዝብና በመንግሥት ይዞታ ሥር የነበሩትን የማዕድን ማምረቻዎችን ፤ የተለያዩ ምርቶች የሚያመርቱ ፋብሪካዎችን፤ የማከፋፈያ ድርጅቶችን፤ ሆቴሎችን፣ የትራንስፖርትና መገናኛ ተቋሞችን ወዘተ በነጻ ገቢያ ሥም ወደ ግል ይዞታ ለማዛወር በሚል ፈሊጥ ያለምንም ግልጽ ጨረታ ገምሱን እራሱ ወደ አቋቋማቸው የንግድ ድርጅቶች ይዞታ በማዛወር የተቀረውን ከአገዛዙ ጋር የቅርብ ግንኙነት ላላቸው ግለሰቦች እዚህ ግባ በማይባል ዋጋ መቸብቸቡ ይታወቃል።

የመንግሥትና የህዝብ ይዞታን ያለምንም ወጪ የግላቸው ለማድረግ የቻሉት የወያኔ ንግድ ድርጅቶች ዛሬ በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ያካበቱ ሲሆን የንግድ ሥራቸውን ለማስፋፋት ከብሄራዊ ባንክ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ ፕራይቬታይዜሽን: በኢትዮጵያ ኪሳራ ሃብታሞች ይበልጥ ሃብታም የሚሆኑበት ሥርዓት

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሃብት ዘርፎ ከሚያዘርፍባቸው በርካታ መንገዶች አንዱ ፕራይቬታይዜሽን ነው።

በመሠረቱ የፕራይቬታይዜሽን ዓላማ በመንግሥት ይዞታነት የተያዙ የማምረቻና የንግድ ተቋማትን ይበልጥ ውጤታማ ነው ተብሎ ወደሚታሰበው የግል ኢኮኖሚ ዘርፍ በማዛወር የገበያ ውድድር እንዲበዛ እና ምርታማነት እንዲያድግ ማድረግ ነው። ፕራይቬታይዜሽን በብዙ አገሮች ተቀባይነት ያገኘው የግሉ ሴክተር በርካታ “ተዋንያን” ያሉበት እና ውድድርም የጦፈበት በመሆኑ በጥራት፣ በዋጋ፣በምርታማነትና በፍትሃዊነት አንፃር ከመንግሥት ሴክተር የተሻለ ነው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ ነው።

በአገራችን ያለው ሃቅ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው።

ወያኔ ፕራይቬታይዜሽንን እየተገበረ ያለው ለሁለት ዋነኛ ዓላማዎች ነው። እነዚህም

አንደኛ፤ የተመረጡ ሃብታሞችን ይበልጥ ሃብታም ማድረግ፤ እና
ሁለተኛ፤ ከብድር ሥርዓት ጋር በማቀናጀት ቀድሞ የረባ ንብረት ያልነበራቸው የሥርዓቱ ደጋፊዎችን በፍጥነት ሃብታም እንዲሆኑ ማድረግ ናቸው።

የወያኔ አገዛዝ ፕራይቬታይዜሽንን ተጠቅሞ ስላደረገው ዘረፋ እና ሕገወጥ የሃብት ክፍፍል በርካታ ማስረጃዎች ማቅረብ ቢቻልም ለዛሬው የሚከተሉትን ብቻ ማንሳት ይበቃል።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር አገስት 1 ቀን 2008 በአዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ለአሜሪካ መንግሥት የላከው ሚስጢራዊ ሰነድ አምልጦ ከሌሎች ብዙ ሰነዶች ጋር ዊኪሊክስ በተሰኘው ድረገጽ ጋር ለሕዝብ ይፋ ሆኗል። በዚህ ሰነድ እንደተገለፀው ወያኔ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ሰነዱ እስከተፃፈበት 2001 ዓም ድረስ ከመንግሥት ወደ ግል ይዞታነት ከተሸጋገሩ ንብረቶች ውስጥ ከእሴት አካያ ስልሳ በመቶው የተዛወሩት ለአንድ ግለሰብ ነው። ይህ ግለሰብ ሼህ መሃመድ አላሙዲን ይባላሉ። ያኔ ሼህ መሃመድ አላሙዲን 64ኛው የዓለም ሃብታም ነበሩ። ከዚያ ወዲህ ደረጃቸውን አሻሽለው ዛሬ 61ኛው የዓለማችን ሃብታም ሆነዋል፤ የብዙዎች የዓለም ሃብታሞች ሃብት ሲቀንስ የእሳቸው ጨምሯል። ለዚህ የኢትዮጵያ ወርቅና ሌሎች ማዕድናት እንዲሁም ሌሎች ቢዝነሶች ሚና የላቸውም ማለት አይቻልም።

ቀሪዎቹ 40 በመቶዎቹን የወሰዷቸውስ እነማን ናቸው? ከላይ የጠቀስነው የአሜሪካ ኤምባሲ ሰነድ እስከ 2001 ዓም ድረስ ፕራይቬታይዝድ ከተደረገው ሃብት 60 በመቶው ለሼህ አሙዲን መሰጠቱን እንጂ ቀሪው 40 በመቶ ለማን እንደተሰጠ የሚናገረው የለም።

በመሠረቱ ስለ ፕራይቬታይዜሽን ለማወቅ የዊኪ ሊክስ ሰነዶችን ማገላበጥ ግዴታ አይደለም። መረጃው ከራሱ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ማግኘት ይቻላል። እኛ እያልን ያለነው ነገር በራሳቸው መረጃ የሚረጋገጥ ነገር ነው።

የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲን መረጃዎች በጥንቃቄ ያጠና ማንም ሰው ቀሪው 40 በመቶ የተሰጠው የሥርዓቱ ምሰሶና ማገር ለሆኑት የትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላትና ምስለኔዎቻቸው መሆኑን በቀላሉ ይደርስበታል።

በአዲስ አበባ ሌሎች ከተሞች እጅግ ዘመናዊ ህንፃዎችን እየገነቡ ሃገሪቷ በእርግጥም ያለፈላት እንዲመስል እያደረጉ ያሉት በብድርና በፕራቬታይዜሽን ሃብታም እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው በዘራቸው የተመረጡ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ናቸው። ብዙዎቹ ከሃያ ዓመት በፊት አንዳችም ሃብት ያልነበራቸው ሰዎች ናቸው፤ ዛሬ ግን ሚሊዮንን ተሻግረው ቢሊየነር የመሆን ህልም ውስጥ ገብተዋል። የእነዚህ ሰዎች የሃብት ምንጭ ከታታሪነትና ከፈጠራ ጋር ምንም ዝምድና የለውም። እነዚህ በሕዝብና በመንግሥት ንብረት የወፈሩ መዥገሮች ናቸው።

የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በዚህ ዓመትም ወደ 30 የሚጠጉ የመንግሥት ድርጅቶትን ሊሸጥ ተዘጋጅቷል። ከእነዚህም ውስጥ ትላልቆቹ የእርሻ ልማት ድርጅቶች ለአላሙዲን ተሰጥተዋል። በቅርብ ዓመታት የጠቀለሏቸው ኩባንያዎች ሲሰሉ የአላሙዲንን የፕራቬታይዜሽን ድርሻ በእሴት ወደ 70 በመቶ አድጓል። አላሙዲን የተውዋቸው በአንፃራዊ መልኩ ትናንሾቹ ኩባንያዎችና ሆቴሎች ደግሞ ለማን መስጠትና በኢትዮጵያ ኪሳራ መክበር እንዳለበት ውሳኔ እየጠበቁ ነው።

በለገጣፎ እና በሌሎችም የአዲስ አበባ አካባቢዎች እንደሚታየው ድሆች ከይዞታቸው እየተፈናቀሉ በራሳቸው መሬት ላይ ለሚገነባ ህንፃ የቀን ሠራተኛ ለመሆን ልመና ውስጥ ገብተዋል። በብድርና በፕራይቬታይዜሽን ጥቂቶች በሃብት ላይ ሃብት ሲያካብቱ በርካታ ድሆች ይበልጥ ደህይተዋል።

ይህ ኢፍትሃዊነት ብቻ አይደለም። ይህንን ዓይን ያወጣ ገፈፋን ማነፃፀር የሚቻለው ከቅኝ አገዛዝ ጋር ነው። የጂኖሳይድ ዎች ዳይሬክተር እንዳብራሩት ሁሉ የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ነው። ወያኔ ኢትዮጵያን ወሮ እንደያዛት አገር ነው እየዘረፈና እያዘረፈ ያለው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በፕራይቬታይዜሽን ስም እየተደረገ ያለውን ግልጽ ዘረፋ አጥብቆ ይቃወማል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሙብቱ፣ ለአገሩ፣ ለሃብቱ፣ ለንብረቱ ሲል ወያኔን ለማስወገድ ቆርጦ ይነሳ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

.......................................................................................................

## ወያኔ በሙስሊም ሃይማኖት ውስጥ የሚያደርገው ጣልቃ ገብነት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ምላሽ እስር፣ ድብደባ እና ዘለፋ ነው። በአገሪቷ ውስጥ ለእምነት መብታቸው በመቆማቸው ብቻ በሺህ የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ወደ ወህኒ ቤቶች ተወርውረዋል።

በሙስሊሙ ላይ የሚደርሰው የሙብት ረገጣ እየከፋ በመጣ መጠን የሙስሊሙ ትግልም እየከረረና እየመረረ መጥቷል። በሣምንታት በፊት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ለወያኔ ቢጫ ቀለም ያለው ወረቀትና ፊኛ በማውለብለብ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸው ይታወሳል።

ሙስሊሙ ለሚያደርገው ሰላማዊ ትግል ተገቢውን ምላሽ እያገኘ ባለመሆኑ ትግሉ ከዚህም በላይ ሊከርና ሊመር እንደሚችሉ የፓለቲካ ተንታኞች እየተናገሩ ነው። እንዲያውም የዒድ በዓልን ምክንያት በማድረግ ትግሊ ከመስጊድ ወደ አደባባይ ሊወጣ ይችላል የሚል አስተያየት ተሰንዝሯል።

የአገራችን ሌላው አቢይ እምነት የሆነው የኦርቶዶክስ ክርስትና አማኒያንም በጳጳስ ሹመት ጉዳይ አጣብቂኝ ውስጥ ገብተዋል። ወያኔ በቀድሞው የወያኔ ጳጳስ ምትክ ሌላ የወያኔ ጳጳስ ለመተካት እያደረገ ያለው ጥረት በርካታ ክርስቲያኖችን እያበሳጨ ይገኛል። የቤተክነት ቀኖና ተጥሶ በጳጳስ ላይ ጳጳስ መሾሙ ሳያንስ አሁን ቀድሞ የተፈጸመው ጥፋት በማረም ፋንታ በጥፋት ላይ ጥፋት እየተደገሰ መሆኑ ክርስቲያኑን በእጅጉ አሳዝኗል።

ስለሆነም ሁለቱ የአገራችንና የዓላማችን ታላላቅ ሃይኖቶች ለሙብቶቻቸው በጋራ የሚቆሙበት ሁኔታ ተፈጥሯል ይላሉ የፓለቲካ ሳይንስ ባለሙያዎች።

የኢትዮጵያ ክርቲያኖችና ሙስሊሞች ሲደጋገፉ መኖራቸው ያስታወሱ እነዚህ ባለሙያ ተንታኞች በተለይ አሁን በተፈጠረው ሁኔታ የሁለቱ ሃይማኖቶች አማኞች መደጋገፍና መቀራረብ ለአገራችን እድገት መልካም አጋጣሚ ሊፈጥር እንደሚችል ያላቸውን እምነት ይገልፃሉ።

## የወያኔ አገዛዝ በፕራይቬታይዜሺን ስም ለግል ባለኃብቶች በሚሸጣቸዉ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ያለምንም ማስያዣ እንዲበደሩ የተደረገውንም የህዝብ ገንዘብ እንዳልከፈሉ ይባስ ብሎም ከስረዋል በሚል ሰበብ ያለባቸው ዕዳ ወደ ልማት ባንክ እንዲዛወር መደረጉ በተደጋጋሚ መዘገቡ ይታወሳል።

የህወሃት መሪዎች የግል ሃብት እንደሆነ ከሚታወቀው ኤፈርት በተጨማሪ የመንግሥትና የህዝብ ሃብት የነበሩትን ድርጅቶች እዚህ ግባ በማይባል ገንዘብ ከተቀራመቱት አንዱ የሆኑት ሼህ አላሙዲን ከመንግስት በጨረታ ለገዟቸዉ ድርጅቶች ምንም አይነት ክፊያ እንዳልፈጸሙ ሪፖርተር የተባለው አፍቃሪ ወያኔ ጋዜጣ ሰሞኑን ከፕራይቨታይዘሽን ኤጀንሲ አገኘሁት ያለውን መረጃ ዋቢ አድርጎ ዘግቦአል። ሼክ አል አሙዲና ሸሪኮቻቸዉ በ2004 ዓም ለገዟቸዉ ለላይኛዉ አዋሽ አግሮ እንዱስትሪ፤ ለቡና ማደራጃና ማከፋፈያ ድርጅት፤ ለአበቦ እርሻ ልማት ድርጅት፤ ለጎጀብ እርሻ ልማትና ኢትዮጵያ እምነበረድ ኢንተርፕራይዝ መክፈል የነበረባቸዉን ቅድመ ክፍያ አሁን ድረስ አለመክፈላቸዉን ሪፖርተር ጋዜጣ አጋልጧል። የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የመቆጣጠር ሐላፊነት የተሰጠዉ የፕራይቬታይዜሺን ኤጄንሲ የስራ ህጎችና መመሪያዎች በግልጽ እንዳስቀመጡት አንድ በኤጄንሲዉ ቁጥጥር ስር የሚገኝ ድርጅት በጨረታ ሲሸጥ ጨረታ አሸናፊዉ በአንድ ወር ግዜ ዉስጥ የጨረታዉን ቅድመ ክፊያ ከፍሎ ማጠናቀቅ አለበት። እነ ሼክ አላሙዲንና የንግድ ጓደኞቻቸዉ ግን ዛሬ ከአንድ አመት በኋላም ለገዟቸዉ አራት ድርጅቶች ቅድመ ክፊያ እንዳልከፈሉ ለማወቅ ተችላል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔ አገዘዝ ትልቁን የአገሪቱን የወርቅ ማዕድን በጨረታ ለግል ባለኃብቶች ለመሸጥ በዝግጅት ላይ መሆኑን ሪፖረተር ጋዜጣ የፕራይቬታይዜሺን ኤጄንሲ ዉስጥ አዋቂ ምንጮችን ገልጾ ዘገበ።ደቡብ ኢትዮጵያ ሻኪሶ ዉስጥ የሚገኘዉ የአዶላ ወርቅ ማምረቻ ማእድን ወርቅ ማምረት ከጀመረበት ግዜ ጀምሮ በመንግስት ይዞታ ስር የቆየ ሲሆን ለረጂም ግዜ ለአገሪቱ አስታማማኝ የዉጭ ምንዛሪ ምንጭ ሆኖ መቆየቱም ይታወቃል።

የወያኔ መሪዎች አለቃቸው መለስ ዜናዊ በሞት ከተለያቸው ወዲህ በህዝብና በመንግሥት እጅ የቀሩትን ድርጅቶች በሙሉ ለመሸጥ ክፍተኛ ጥዲፊያ ላይ መሆናቸውን ላለፈው አንድ ወር በማከታተል እየወጡት ካለው የጨረታ ማስታወቂያ ጋጋት ለማወቅ ተችሎአል። ወያኔዎች ድርጅቶቹን ለመሸጥ እየተጣደፉ ያሉት የሥልጣን ዕድሜያቸው እያጠረ መምጣቱ ስላሳሰባቸው ከሽያጩ የሚገኘውን ገንዘብ ዘርፈው ለመሰወር በማሰብ ነው የሚሉ ውስጥ አዋቂዎች አሉ።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

# ስልጣንን ከኦርቶዶክስ እና ከአማራ ነጥቅናት !!!

**“የስብሃት ነጋ ቅኔ”**

ህወሃት ጠላቶቼ ናቸው ብሎ ከሚቆጥራቸው መካከል ዋነኞቹ የአማራ ህዝብና፤ የኦሮቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ናቸው። እዚህ ላይ “ተፈጥሮና አማራ የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላቶች ናቸው” ብለው ጽፈው የተማማሩበትን ማስታወስ ያስፈልጋል። ኦሮቶዶክስ ቤተክርስትያን እያለችም እቅዳችንን ማስፈጸም አንችልም ባሉት መሠረትም ቤተክርስትያኒቷን ለሦስት እንድትከፈል ማድረጋቸውም የሚዘነጋ አይደለም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከቂምና በቀል በስተቀር ፍቅርን የማያውቀው እና በእርጅና ዘመኑ እንኳ ራሱን መግራት ያቃተው ስብሃት ነጋ የተባለው ክፉ ዘረኛ በቅርቡ “ስልጣንን ከኦሮቶዶክስና ከአማራ እጅ ነጠቅናት ይህም የትግላችን ውጤት ነው” ማለቱን ሰምተናል። ባለፉት አርባ ዓመታት የትኛው አማራ፤ የትኛው ኦሮቶዶክስ ስልጣን ይዞ ነበር ቢባል ግን መልስ የለውም። የከሃዲው ስብሃት ነጋ አባባል ግን ለአማራ ህዝብና ለኦሮቶዶክስ ቤተክርስትያን ያለውን ሥር የሰደደ ጥላቻ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። መለስ ዜናዊም በህይወት ዘመኑ ለቤተክርስትያኒቷና ለአማራ ህዝብ ባለው ጥላቻ መሠረት ቤተክርስትያኒቷን ለማፍረስ የቻለውን ሁሉ አድርጓል። የአማራንም ህዝብ ለማጥፋት ብዙ አረመኔያዊ ተግባራትን ፈጽሟል። በእርሱ የአገዛዝ ዘመን ከሁለት ሚሊዮን በላይ አማራ ከቁጥሩ ጎድሎ የት እንደገባ ሳይታወቅ ቀርቷል።

ከሁለት ሚሊዮን በላይ የአማራ ህዝብ የት ገባ ተብሎ የተጠየቀው መለስ ዜናዊ ያለምንም እፈረትና ታሪክና ሰው ምን ይለኛል ሳይል “በኤድስ አልቋል” ብሎ በድፍረት መልስ ሰጥቷል።ይሄ በጣም አሳፋሪ እና ነውር ነገር ነው። በተለይም አገርን እመራለሁ ብሎ በህዝብ አናት ላይ ከተቀመጠ ሰው አንደበት ሲወጣ። ህወሃቶች እንዲህ ያለውን አሳፋሪንና ነውር ነገረን ለይተው አያውቁም ማለት አይቻልም። አንድን ህዝብ ለይተው “በኤድስ አለቀ” ብሎ መናገር ነውር መሆኑን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ነውር መሆኑን እያወቁ እንዲህ ያለ አሳፋሪ ነገር በአደባባይ እንዲናገሩ የሚያደርጋቸው በእድሜም ሆነ በትምህርት መገራት ያልቻለው ትእቢታቸውና በአጠቃላይ ለአማራ ህዝብ ያላቸው ሥር የሰደደ ጥላቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ህወሃት ራሱን የአማራ ህዝብ ጠላት ነኝ ብሏል። ህወሃትን ጠላት አይደለም ብሎ መከራከር እማይቻልበት ደረጃ ላይም ተደርሷል።በጋምቤላ እና በኦጋዴን ላይ የተፈፀመው ግድያ በዘር ማጥፋት ወንጀል ውስጥ ተመድቧል። በኦሮሞ እና በደቡብ ህዝቦች ላይ የተፈፀመውን ወንጀል ዘርዝረነው አንዘልቅም። የህወሃት ህልም በማንኛውም መንገድ ስልጣኑን ይዞ እርሱና እርሱ የፈቀደላቸው ብቻ ሲኖሩ ሌላው የእነርሱ አናኗሪ ሁኖ እንዲኖር ነው። ህልምና ራዕያቸውም እነርሱ የበላይ ሌላው የበታች ተኩኖ የሚኖርበት ሥርዓት እንዲገነባ ነው።እንዲህ ያለ ነገር አይጠቅምም የሚለውን ሁሉ አሸባሪ እና ጠላት ነው ብለው የቻሉትን ገድለዋል፤ ለመግደል ያልቻሉትንም የእድሜ ልክ እስራት ፈርደዋል።ይሄ ሁሉ ተደምሮ የሚያሳየን ህወሃቶች የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች መሆናቸውን ነው እንጂ ወዳጆች መሆናቸውን አይደለም። እንግዲህ ትግሉም መቀኘት ያለበት ከዚህ አቅጣጫ መሆን ይኖርበታል።

እናንተ እየመራችሁኝ እኔ እየተከተልኳችሁ እንዘልቃለን ያለው ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የተባለው ግለሰብ በጠቅላይ ሚንስትርነት ከተመደበ በኋላ የህወሃት አባት ነው የሚባለው ስብሃት ነጋ “ስልጣንን ከኦርቶዶክስና ከአማራ ነጠቅናት” ብሎ መናገሩ ለአማራው ህዝብ እና ለኦሮቶዶክስ ቤተክርስትያን ያለውን ጥላቻ ከማሳየት በቀር ያሳየው በጎ ነገር የለም። ስብሃት ነጋም ሊነግረን የፈለገው መልእክት ለአማራና ለቤተክርስትያኒቷ ያለውን ጥላቻ እንጂ ፍቅርን አይደለም። ይሄ ማለት ሌሎችን ህዝቦች ይወዳል ማለት አይደለም። አሁንም ደግመን እንናገራለን ይህ ግለሰብና ቡድኑ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ናቸው።

ህወሃት እንደ ህዝብ አማራን፤ እንደ ድርጅት ኦሮቶዶክስ ኃይማኖትን ለማጥፋት የጭካኔ ሰይፉን ከሰገባው የመዘዘው ገና ድሮ ሕፃን ሳለ መሆኑ ይታወቃል። ባለፉት ሃያ አንድ ዓመታት የአማራን ህዝብ ቀጥቅጠዋል፤ አዋርደዋል፤ ገድለዋል፤ አሳደዋል፤ ለርሃብና ለእርዛት ዳርገዋል። በአማራ ህዝብ ላይ የተነዛው የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ እና የተፈፀመው ወንጀል መቼም መቼም የሚረሳ አይደለም። በተመሳሳይ ሁኔታ ኦሮቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንን የዘረኞችና የአመንዝሮች መጫወቻ አድርገዋታል። አሁን ደግሞ አንድነቱን ጠብቆ ለብዙ ዘመን የኖረውን የሙስሊሙን ማህበረሰብ ለመበጥበጥ የጥፋት ሰይፋቸውን መዘዋል። በኦሮቶዶክስ ቤተክርስትያን ላይ አባ ገ/መድህንን በመሾም ቤተክርስትያኒቷን እንዳዋረዷት ሁሉ በሙስሊምሙ ላይ ታማኝ ካድሬያቸውን በመሾም የምእመኑን አንድነት ለማፍረስ ሌተ ተቀን እየማሰኑ ይገኛሉ። ይሄ ድንቁርና የወለደው ትዕቢት የሚተነፍስበት ግዜ ግን እሩቅ አይሆንም።

የተከበራችሁ ወገኖቻችን !

ህወሃቶች ከጥፋታቸው መመለስ የሚችሉ አይደሉም። የህዝቡን ትእግስት እንደፍርሃት ቆጥረው “ሽንታም” ብለው ከመሳደብ ተመልሰው ወደ ልቦናቸው የሚመጡ አይደሉም። ካለኛ ጀግና ካለኛ ሰው የለም ብለውም የእኛን እድል ፈንታ ወሳኞች እነርሱ ሁነዋል። ኢትዮጵያዊያንም እነርሱ ሲፈቅዱ የሚኖሩ፤ እነርሱ ካልፈቀዱለትም መኖር የማይችሉ ዜጎች ሁነዋል። እኛ ወርቅ አንተ ግን ወርቅ ያልሆንክ ብለው በአደባባይ መናገራቸውንም በትዝብት ተመለክተናል።እንግዲህ እስከ መቼ በህወሃቶች ፈቃድ እንኖራለን ?እስከመቼስ እነርሱ ለይተው በወሰኑልን መንገድ እንጓዛለን ?እንዴትስ የእነርሱ አኗኗሪ ሁነን እንዘልቃለን?

የተከበራችሁ ወገኖቻችን ሆይ !

አሁን ለራሱ ክብር የሚሰጥ ዜጋ ትክክለኛውን መልስ ይፈልግ።ትክክለኛዋ መልስ ከሂሊናችን ማህደር ውስጥ አለች።እርሷም “ ነፃነት ወይም ሞት ! ” የምትል ነች።

ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና የዴሞክራስ ንቅናቄ ለጥያቄዋ መልስ አግኝተን ነፃነት ወይም ሞት ካልን ቆይተናል።ህወሃቶች ተጭነውን እኛ ተሸከመናቸው አብረን ልንኖር አንችልም። እነርሱም ሳይጫኑን እኛም ሳንሸከማቸው በነፃነት የምንኖርባት ኢትዮጵያ እስከምትፈጠር ድረስ የምር ከመታገል ውጪ ሌላ አማራጭ አለ ብለን አናምንም።ስለዚህ የጀመርነውን ትግል በጀመርነው መንገድ አጠናክረን እንቀጥላለን። ህወሃቶች የተመረኮዙት የሸንበቆ ምርኩዝ ተሰብሮ የነፃነት ጎህ እስኪቀድ ድረስ ሳናፈገፍግ እንታገላለን። እናሸንፋለንም።ያን ግዜም ስልጣንን ከዚህ ህዝብ ከዚያ ህዝብ ነጠኳት የሚል ትዕቢተኛ አይኖርም።ስልጣን ከኢትዮጵያ ህዝብ የሚሰጥ እንጂ የሚነጠቅ አይደለም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## በእስር ላይ የሚገኙት እነ አንዱዓለም አራጌ አሸባሪ ሳይሆኑ ለዚች ሀገር ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የሚደክሙ የነጻነት አርበኞች ናቸው ሲሉ በወያኔ ምክር ቤት ብቸኛው የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ ገለጹ

ከ547 የወያኔ ምክር ቤት አባላት ብቸኛ ተቃዋሚ የሆኑት አቶ ግርማ ሰይፉ ይህንን የገለጹት በቅርቡ በበረከት ስምኦን ተዘጋጅቶ በይስሙላው ፕሬዝዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ለፓርላማው ቀርቦ በነበረው ያለፈው በጀት ዓመት የሰራ ክንዋኔና የቀጣዩን በጀት ዓመት እንቅስቃሴ በሚጠቁመው ሪፖርት ላይ በሰጡት አስተያየት ነው።

አቶ ግርማ ያቀረቧቸው ሐሳቦች በሁለት የተከፈሉ ሲሆኑ በፕሬዚዳንቱ ንግግር ውስጥ ሊካተቱ የሚገቡና ሊካተቱ የማይገቡ በሚል የቀረቡ ነበሩ።

በዚህም መሰረት ከእስረኞች መፈታት ጋር በተያያዘ ደረቅ ወንጀል የሠሩትን ታራሚዎች ብቻ መፍታት ሳይሆን የአሸባሪነት ታፔላ ተለጥፎ የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞችንና ጋዜጠኞችን ለመፍታት የሚያስችል አቅጣጫ መቀመጥ አለበት የሚል ፅኑ እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

በማያያዝም በደረቅ ወንጀል ታራሚዎች መለቀቅ ላይ ተቃውሞ እንደሌላቸው በመግለጽ ነገርግን በሀሰት የሽብርተኝነት ክስ ተወንጅለው አላግባብ የታሰሩት ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የሚደክሙት የነጻነት አርበኞች አለመካተት ግን ተገቢ አለመሆኑን አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም በሀገሪቱ የአንድ ፓርቲ የበላይነት መስፈንና የፖለቲካ ምኅዳሩ መጥበብም በንግግሩ ውስጥ መካተት ይገባቸዋል ብለዋል።

በሌላ በኩል በይስሙላው ፕሬዚዳንት በተነበበው የነበረከት ስሞን ሪፖርት ውስጥ በየቦታው መለስ ዜናዊን የሚመለከቱ ሐረጐች መካተታቸው አላስፈላጊ ከመሆናቸውም ሌላ ገዥውን ፓርቲ በቀጣይ በሚደረግ የአፈጻጸም ግምገማ በሚፈጠር ጉድለት፣ ይህ ዕቅድና ሐሳብ የእኛ ሳይሆን የመለስ ነበር በማለት ከተጠያቂነት ለመሸሽ ያቀደ ያስመስለዋል በማለት መለስን የሚመለከቱ ሐረጐች እንዲወጡ የጠየቁ ሲሆን ሌሎች በርካታ ጉዳዮችንም አንስተዋል፡፡

በመጨረሻም አዲሱ የወያኔ ጉዳይ አስፈጻሚ ሀይለማሪያም ደሳለኝ የአነጋገር ዘይቤውን እንኳን የመለስን ለማስመለስ በመጣር ሁሉንም የአቶ ግርማ ጥያቄዎች ውድቅ አድርጓቸዋል።

## በወያኔ አገዛዝና በኦጋዴን ነፃነት ግንባር መካከል ናይሮቢ ዉስጥ ተጀምሮ የነበረዉ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የድርድሩን መቋረጥ አስመልክተዉ ለኢሳት ቴሌቪዥን ቃለ መጠይቅ የሰጡት አቶ አብዱራሂም ማህዲ አኛ የፈለግነዉ በእኩልነትና በመተማመን ላይ የተመሰረተ ዉይይት ሆኖ ሳለ ወያኔ ድርድሩን በእሱ የበላይነት እንዳሰኘዉ መምራት በመጀመሩ ያአሁኑን ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም ሊኖሩ የሚችሉ ዉይይቶችን አደናቅፏል ብለዋል። የወያኔ አገዛዝ ከኦብነግ ጋር ዉይይት አደረግን ሲል ይህ የመጀመሪያ ግዜዉ አለመሆኑንና ከዚህ ቀደም ወያኔ ኦብነግ ጠመንጃዉን አስቀምጦ በሰላማዊ መንግድ አገር ለመገንባት ቅርጦ ተነስቷል ብሎ በተደጋጋሚ መለፈፉ ይታወቃል፤ ሆኖም ይህ በሆነ በጥቂት ቀናት ዉስጥ ኦጎዴን ዉስጥ አገዛዙ ከኦጋዴን አማጽያን ጋር የተኩስ ልዉዉጥ ማድረጉን አለም አቀፍ የመገናኛ አዉታሮች መዘገባቸዉ ይታወሳል።

## አንድ ታዋቂ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና ሬድዮ ጋዜጠኛ በቃኝ ብሎ ከስራዉ ተሰናበተ - ኢቲቪ “የቆሻሻ ፕሮፓጋንዳ ፋብሪካ” ነዉ ሲል የቀድሞ መስሪያ ቤቱን አጋለጠ

ለረጂም ግዜ በኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ዉስጥ በጋዜጠኝነት ሙያ ሲያገለግል የነበረዉ ጋዜጠኛ ሠለሞን መንግስቱ በቆሻሻ የወያኔ ፕሮፓጋንዳ አገርንና ህዝብን ማታለል በቃኝ ብሎ ከስራዉ መሰናበቱንና ለግዜዉ በዉል ተለይቶ ወዳልታወቀ ቦታ መሄዱን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኘዉ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ ገለጸ።

ጋዜጠኛ ሠለሞን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በተለይ በእንግሊዝኛዉ መምሪያ ዉስጥ የተለያዩ ፕሮግረሞችን አዘጋጅቶ ያቀርብ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት አለኝ ከሚላቸዉ ጥቂት ታዋቂና በሳል ጋዜጠኞች አንዱ አንደነበር ለማወቅ ተችሏል። ጋዜጠኛ ሠላሞን ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ዉስጥ የኤዲቶሪያል ነፃነት አለመኖሩን ገልጾ የድርጅቱ የአማርኛም ሆነ የእንግሊዝኛ ክፍሎች የሚሰሯቸዉን ዋና ዋና ስራዎች ሁሉ የሚሰሩት የአገዛዙ የፖለቲካ ካድሬዎች በቅርብ እየተገኙ በሚሰጧቸዉ መመሪያ መሆኑን አጋልጧል።

ጋዜጠኛ ሠለሞን መንግስቱ ስራዉን በይፋ የለቀቀዉ “በቃ ማለት በቃ” ነዉ ዳግም ወደዚህ የቆሻሻ ፕሮፓጋንዳ ማምረቻ ድርጅት አልመለስም የሚሉና የአገዛዙን ባለስልጣኖች እጅግ ያስቆጡ ጽሁፎችን በፌስ ቡክ ገጹ ላይ ካሰፈረ በኋላ መሆኑን ከጋዜጣኛዉ የግል ፌስ ቡክ ላይ ከተገኙ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል።

ጋዜጠኛ ሠለሞን በወያኔ የፕሮፓጋንዳ መዋቅር ዉስጥ ቁልፍ ስራዎችን ሲሰራ መቆየቱ እጅግ በጣም እንዳሳዘነዉ ገልጾ ከአሁን በኋላ የረጂም ግዜ የጋዜጠኝነት ልምዱን በመጠቀም ለኢትዮጵያ ህዝብ ትክክለኛ መረጃዎችን ለማቅረብ ቃል ገብቷል። ከዚህ በተጨማሪ የኢቲቪ ጋዜጠኞች አማራጭ አጥተዉ ነዉ አንጂ የብዙዎቹ ፍላጎት ህዝብን ማገልገል እንደሆነ ገልጿል።

## አራቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች በስልጣኝ ይገባኛል እየተፋጩ ነዉ - ህወሀት የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ለኔ ይገባኛል ብሏል

ከ1983 እስከ 2002 ድረስ ለ19 አመታት የጠ/ሚኒስትርነቱን፤ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱንና ሌሎችንም ቁልፍ የስልጣን ቦታዎች ለብቻዉ ቆንጥጦ ይዞ የነበረዉ ህወሀት ቁንጮውን በሞት ከተነጠቀ ወዲህ ዘንድሮ ምግቡን እንደተቀማ ልጅ ጭቅጭቅ መጀመሩንና በተለይ ከባዕዴንና ከኦህዴድ ጋር የስልጣን ይገባኛል ፍጭት ዉስጥ መግባቱን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ምንጮች ገለጹ።

በአንድ በኩል የኢትዮጵያን ህዝብ የስልጣን ባለቤት ያደረግነዉ እኛ ነን በሚሉ ባዶ ቃላት እራሱን የሞላዉና በሌላ በኩል ደግሞ 17 አመት ተዋግተን ደርግን ያሸነፍነዉ እኛ ነን በሚል አብሪት የተወጠረዉ ወያኔ የአገሪቱን ኤኮኖሚ፤ ጦር ኃይሎች፤ ፖሊስ ሠራዊትና የደህንነት ኃይል መቆጣጠሩ አንሶት የዉጭ ጉዳይ ሚነስትርነት ቦታ ለኔ ይገባኛል በሚል ስግብግብ ጥያቄ ኃ/ማሪያም ደሳለኝን ማስጨነቅ መጀመሩ በህወሀትና በባእዴንና በተለይ በኦህዴድ መካከል ያለዉን የሻከረ ግንኙነት የባሰ ያበላሸዋል እያሉ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች በመናገር ላይ ናቸዉ።

የኃ/ማሪይም ደሳለኝና የደመቀ መኮንን ጠ/ሚኒስትርና ምክትል ጠ/ሚኒስትር ሆኖ መሾም ዲሞክራሲያዊ አሰራርን የተከተለ ሚዛናዊ አሰራር አይደለም የሚል ከፍተኛ ተቃዉሞ በኦህዴድ ዉሰጥ በመሳማት ላይ ባለበት በአሁኑ ወቅት የበረከት ስሞዖን ቡድን ከበስተኋላ ሆኖ እያሽከረከረው መሆኑ የታወቀው ኃ/ማሪይም ደሳለኝ የህወሀቱን ብርሀኔ ገብረክርስቶስን የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር አድርጎ ለመሾም በዝግጅት ላይ መሆኑ ለማወቅ ተችሎአል። ከ ኢህአደግ አባል ድርጅቶች ውስጥ ብአዴንና ህ የድህሬ መለስ ዜናዊ የሥልጣን ክፍፍል ለማስመሰልም ቢሆን የባሳ የሚያስከፋና በመጠኑም ቢሆን ህወሀትን የሚያስደስት አካሄድ ገዢዉን ፓርቲ ኢህአዴግንም ሆነ የኃ/ማሪይም ደሳለኝን መንግስት እንደሚያዳክምና አገሪቱን ቀፍተኛ ዉስጥ ሊከትታት እንደሚችል የአዲስ አበባዉ ዘጋቢያችን የድፕሎማቲክ ምንጮችን ጠቅሶ በላከልን ዜና ገለጸ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኃ/ማሪይም ደሳለኝ የጠ/ሚኒስትርነቱን ቦታ እንዲይዝ ከፍተኛዉን ሚና አንደተጫወተ በሚነገርለት በበረከት ስሞኦንና ኃ/ማሪይም እንዳይሾም ሽንጧን ገትራ በተሟገተቻዉ በአዜብ መስፍን እንዲሁም በሁለቱ ደጋፊዎች መካከል የሚካሔደዉ የዉስጥ ለዉስጥ የፖለቲካ ጦርነት አሁንም እንደቀጠለ መሆኑን ምንጮቻችን ከአዲስ አበባ የሚልኩልን ዜናዎች ያስረዳሉ። አዜብ መስፍን ኃ/ማሪያም ደሳለኝን ምክትል ጠ/ሚኒስትር በነበረበት ግዜም ለማዘዝ ትሞክር እንደነበርና በሀለቱ መካከል መካከል ለረጂም ግዜ የቆየ ሽኩቻ እንደነበረ ይታወቃል። አዜብ መስፍን በሏ ከሞተ ከሁለት ወራት በኋላና አዲስ ጠ/ሚኒስትር ከተሾመ ከሦስት ሳምንታት በኋላም በእብሪትና በአወቅኩሽ ናቅኩሽ ከቤተ መንግስት አልወጣም ማለቷ የዚሁ ሽኩቻ ዉጤት እንደሆነ ይነገራል። ይህ የአዜብ መስፍን እብደት የተቀላቀለበት እምቢታ በአለም ታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ ተራ ግለሰብ ቤተ መንግሰት ዉሰጥ እየኖረ የአገር መሪ ከህዝብ ጋራ እየተጋፋ እንዲኖር የሚያደርግ አሳዛኝና የአገርን ክብር የሚነካ ሁኔታ ፈጥሯል በማለት ብዙ ኢትዮጵያዉያን ድርጊቱን በመኮነን ላይ መሆናቸዉን ዘጋቢያችን አክሎ የላከልን ዜና ያስረዳል።

## የኢትዮጵያ የዉጭ ዕዳ ቁልል መጠን እጅግ በጣም በሚያስፈራ መልኩ እያደገ መሄዱን የአገዛዙ የገንዘብና የኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ጽ/ቤት አመነ

የኢትዮጵያ የገንዘብና የኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ባለፈዉ ሳምንት መገባደጃ አዲስ አበባ ዉስጥ ይፋ ባደረገዉ መረጃ መሰረት የኢትዮጵያ የዉጭ ዕዳ መጠን በሚያስፈራ መልኩ እያሻቀበ ሄዶ ከአገሪቱ የመክፈል አቅም በላይ መድረሱ ታወቀ። በቅርቡ 134 ቢሊዮን ብር የነበረዉ የአገሪቱ የዉጭ ዕዳ መጠን በትንሽ ግዜ ዉስጥ 200 ቢሊዮን ብር መድረሱንና ይህ መጠን ኢትዮጵያ በቅርቡ ከቻይና የተበደረችዉን 51 ቢሊዮን ብርና ከኤክሲም ባንክ የተበደረችዉን 5.1 ቢሊዮን ዶላር እንደማይጨምር ታዉቋል። ከዚህ በተጨማሪ ባለፉት አራት አመታት በእድገትና ትራንስፎርሜሺን ሰበብና በህዳሴዉ ግድብ ስም አገዛዙ ከአገር ዉስጥ ባንኮች ከ60 ቢሊዮን ብር በላይ መበደሩ የሚታወቅ ሲሆን እዚህ መጠን ላይ ህዝቡ እየተገደደ የሚገዛዉ ቦንድ መጠን ሲጨመርበት የአገር ዉስጥ ዕዳዉ መጠንም ቢሆን በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ የአለም ባንክና አይ ኤም ኤፍ በቅርቡ ማስጠንቀቃቸዉ የሚዘነጋ አይደለም።

የግንቦት ሰባት ድምፅ ዘጋቢ ያናገራቸዉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኤኮኖሚክስ ፕሮፌሰር አንደተናገሩት የኢትዮጵያ መንግስት የተበደረዉ ገንዘብ አደገኛነቱ መታየት ያለበት ከብዛቱ አንጻር ብቻ ሳይሆን የአገሪቱን የኢንቨስትመንት ካፒታል ከማራቆቱ አንጻር ሊሆን ይገባል ብለዋል። መንግስት ከአቅሙ በላይ በተበደረ ቁጥር በአንድ በኩል መጪዉን ትዉልድ ዕዳ ከፋይ የሚያደርገዉ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የአገር ዉስጥ እንቨስተሮች ለልማት መበደር የሚችሉትን ካፒታል በመሻመት የአገሪቱን እድገት ሊያንቀዉ እንደሚችል እኚሁ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የፈለጉ የኤኮኖሚክስ ፕሮፌሰር ተናግረዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከዉጭ የተገኘዉ የብድር መጠንና ለበድሩ በየአመቱ የሚከፈለዉ ከፍተኛ የወለድ መጠን አዲስ አበባ ዉስጥ በየቦታዉ የህዝብ መነጋገሪያ መሆኑን የአዲስ አበባ ምንጮቻችን ገለጹ። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከወጭ ለተበደረችዉ ብድር በየአመቱ አምስት ቢሊዮን ብር በወለድ መልክ አንደምትከፍል ለማወቅ ተችሏል። በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔ ባለስልጣናትና ቤተሰቦቻቸዉ አገሪቱ ከዉጭ አበዳሪዎች ከተበደረቸዉ ገንዘብ በላይ ወይም ከ221 ቢሊዮን ብር በላይ ከአገር አሸሽተዉ አዉሮፓና ታይላንድ ዉስጥ በሚገኙ ባንኮች ዉስጥ ማከበታቸዉ በተደጋጋሚ የተነገረ መሆኑ ይታወቃል።

## ዜጎችን አፈናቅሎ የከተማ ቦታን መቸብቸብ አሁንም እንደቀጠለ ነው ። ለዚህ ተግባር መርካቶ ውስጥ ሁለት መንደሮች ሆን ተብሎ በ እሳት እንዲጋይ ተደርጎአል

የመለስ ዜናዊን ርካሽ ተግባራት እንዳሉ ይዤ እቀጥላለሁ የሚለው የወያኔ ቡድን የተለመደውንና ያፈጀውን የመለስ ዘዴ በመጠቀም በተለምዶ ምን አለሽ ተራና አሜሪካን ግቢ እየተባሉ ከሚጠሩት አካባቢዎች ነዋሪዎችን በማፈናቀል መሬቱን ለመቸብቸብ አካባቢዎቹን በእሳት ማጋየቱ ተነገረ።

የግንቦት 7 ዘጋቢ ያነጋገራቸው በየአካባቢዎቹ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች በምሬት ሲገልጹ ቃጠሎው ሆን ተብሎ እንዲነሳ ካልተደረገ በስተቀር ሊነሳ የሚችልበት አንዳችም ምክንያት የለም። ከልምድ እንደምናውቀው ይህ ተግባር የወያኔ መንግስት የደከመ ስልት ነው። ይህንን የወረደ ስራ እኛም እናውቃለን ፤እነሱም እንደምናውቅ ያውቃሉ፤ ነገርግን ምን ያመጣሉ የሚለው የወያኔ ትእቢት ውጤት ነው ብለዋል።

የእሳት አደጋ መከላከያ መኪኖች ዘግይተው ከመድረሳቸውም ሌላ አንዳችም እርዳታ አለማድረጋቸውን የሚናገሩት በአሜሪካን ግቢ አካባቢው የነበሩ ሰዎች፣ ባገኙት እቃ ውሃ በመርጨት ከብዙ ጥፋት በኋላ ሊያጠፉት መቻላቸውን አስረድተዋል።

አንድ የተቃዋሚ ድርጅት አባል በበኩላቸው አዲሳቹ የወያኔ አለቆች ህዝቡ ለመለስ ዜናዊ በማዘን በእሱ ዘመን ይፈጸሙ የነበሩ ወንጀሎች ሁሉ መቀጠል አለባቸው የሚል መልእክት አስተላልፎልናል ያሉትን ፌዝ ወደ ምር በመቀየር የህዝቡን አበሳ ይበልጥ ማባባስ መቀጠላቸው እንዳሳዘናቸው ለዘጋቢያችን ገልጸዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org